# የጥቁሮች የነፃነት ተምሳሌት

እ.ኤ.አ በ1880ዎቹ መጀመሪያ ጀርመን አገር በርሊን ከተማ ላይ በተደረገው የአውሮጳ ቅኝ ገዢ መንግስታት ስብሰባ ላይ "ጥቁር ሰው ትልቅ ትል ነው፤ቅንቡርስ ነው እንጂ ነፍስ ያለው ሰው አይደለም"ብለው የሰውን ልጅ እንደነፍሳት በመቁጠር በእብሪት ተወጥረው ተሳለቁበት፡፡ "ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ…" እንደሚባለው አፍሪካውያንን በዚህ ልክ ወደ ማዋረድ የገቡት አፍሪካ አህጉርን ለመቀራመት በማሰብ ነው፡፡

ኢጣሊያ አንዱ የበርሊን ስብሰባ ተሳታፊ የአውሮጳ ቅኝ ገዢ መንግስት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዚያ ዘመን የቅኝ ግዛት ቀንበሩን ሊጭንባቸው ከከጀላቸው አገሮች መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ነበረች፡፡ በመሆኑም የቅኝ ገዥተገዥ መደባባት ድራማው ማሟሟቅ የጀመረው እንግሊዝ ምስራቅ አፍሪካን በተለይም የዓባይ ወንዝ ተፋሰስን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ካላት ፍላጎት በመነጨ የውሃ ዲፕሎማሲ እንደሆነ ጥቂት የቅኝ ግዛት ጦርነት ታሪክ ፀሐፍት ይገልፃሉ፡፡ ይህ ታሪክ እንግሊዝ ግብፅን ቅኝ በገዛችበት ወቅት የአባይን ውሃ በብቸኝነት ጠቅልላ በመያዝ ሱዳን ለመስኖም ይሁን ለሌላ ፕሮጀክት ከአባይ ውሃ እንዳትጠቀም ከማድረጎ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በቀያቸው አለፍ ሲልም በቤታቸው በር ላይ እየደነፋ ለዘመናት ሲፈስ ከኖረው አባይ ውሃ እንዳትጠቀሙ ተብለው ያውም መጤ በሆነው እንግሊዝ ተከልክለው የበይ ተመልካች የሆኑት ሱዳኖች "ከዘላለም ባርነት የአንድ ቀን ጌትነት" ይሻለናል ብለው በቅኝ ገዥዋ እንግሊዝ ላይ የከበባ ጦርነት ከፈቱ፡፡

እንግሊዞችም በሱዳኖች የደረሰባቸውን ከበባ ለመቋቋም ከኢትዮጵያዊው ንጉሠ ነገሥት አፄ ዮሐንስ ጋር የሒዎት ስምምነትን ተፈራረሙ፡፡ ስምምነቱ በሱዳን ከበባ የተፈተፀመባቸው ቅኝ ገዥዎቹ እንግሊዞች በኢትዮጵያ በኩል አድርገው በሰላም መውጣት እንዲችሉ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ነበር፡፡ እንግሊዝ በበኩሏ ለኢትዮጵያ ወደቦችን ክፍት ለማድረግ በሒዎት ውል ላይ ተስማምታለች፡፡ እንግሊዝ ግን ለኢትዮጵያ የገባችውን ቃል አጥፋ በተቃራኒው ምስራቅ አፍሪካ ውስጥ ተገዳዳሪ ሆና የመጣችባትን ፈረንሳይን ለመግታት ኢጣሊያን ጋበዘቻት፡፡ ኢጣሊያ በእንግሊዝ ግብዣ የገባችበት የወዲያው ምክንያት ፈረንሳይን መግታት የሚል ቢሆንም የሮም ቄሳር ኃይላት ግን የራሳቸውን ቀመር በአባከሳዊ ስሌት እያሰሉ ኢትዮጵያን ቅኝ ለመግዛት ወደ መከጀል ገቡ፡፡ ይህን የተረዳችው እንግሊዝ ኢጣሊያ ከአፄ ምኒልክ ጋር የውጫሌ ስምምነት እንድትፈራረም አደረገች፡፡ **ያ ስምምነት ግን በመርዝ የተለወሰ ሀረግ እና አንቀጾችን ይዞ ነበር፡፡ በዚህ ውል አንቀጽ 17 ላይ በጣሊያንኛ የሰፈረው ጽሑፍ ኢትዮጵያ ከአውሮፓ መንግሥታት ጋር ማድረግ የምትፈልገውን ግንኙነት በጣሊያ በኩል መሆን እንዳለበት**

ሲያመለክት የአማርኛው ግንግኙነቱን በኢጣሊያ በኩል ማድረግ ትችላለች ይላል። ይህ የትርጉም ልዩነት

እንደታወቀ መጀመሪያ ላይ አጼ ምኒልክ የውሉን አንቀጽ 17 እንደማይቀበሉ ካሳወቁ በኋላ ቀጥሎም የውጫሌውን ውል ሙሉውን ውድቅ አደረጉት። ይህም ለዓድዋው ጦርነት ዋነኛ ምክንያት ሆነ። ለጦርነቱ መነሻ የሆነው ውል የተፈፀመው ከአዲስ አበባ በስተሰሜን 468 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ውጫሌ ከተማ ግርጌ ከአምባሰል ተራራ ሥር ወሎ ውስጥ ንጉሥ ይስማ እየተባለ በሚጠራ ሥፍራ ነው።

የውጫሌ ስምምነት መፍረስን ተከትሎ ኢጣሊያ ሠራዊቷን ለወረራ ማንቀሳቀስ ጀመረች። ከኢትዮጵያ በኩልም የአጼ ምኒልክን ጥሪ ተከትሎ ከመላዋ አገሪቱ የተሰባሰበው ሠራዊት አገሩን ከኢጣሊያ ወረራ ለመከላከል ያለውን መሳሪያ ይዞ ወደ አድዋ አቀና። አድዋ ከአዲስ አበባ ወደሰሜን ኢትዮጵያ ስንሄድ 1066 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ታላቁ ጦርነት የተደረገበትሥፍራ ነው። ሶሎዳ ተራራ፤ማርያም ሸዊቶ፤አዲተቡን፤እግዚሃር አሳየ፣የሚባሉ ገመገሞችና ተራራማ ሥፍራዎችም ዋነኞቹ የጦር ግንባሮች ነበሩ።

“ለጦርነቱ በአጼምኒልክ የተመራው ሠራዊት 29 ሺህ ፈረሰኞችን ጨምሮ እስከ 120 ሺህ የሚገመት አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር በባዶ እግሩ የተጓዘ የኢትዮጵያ የገበሬ ሠራዊት በወታደራዊ አካዳሚ የሠለጠነውን የኢጣሊያ ወራሪ ጦር የካቲት 23 ማለዳ አሥራ አንድ ሰዓት ግድም ገጥሞ ከረፋዱ አራት ሰዓት ላይ ማሸነፉን አረጋግጧል” ይለናል የታሪክ ተመራማሪው ጆርጅ በርክሌይ የአድዋ ጦርነትና ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ በተሰኘውና ዳኘው ኃይለሥላሴ ወደ አማርኛ በተረጐሙት መጽሐፉ ላይ። በዚህ ድብልቅልቅ ያለ ውጊያ ከ56 የኢጣሊያ መድፎች በተጨማሪ ብዙ ሺህ ቀላልና ከባድ መትረየሶች እንዲሁም የነፍስ ወከፍ ጠመንጃዎች በአሥር ሺዎችና በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩ መሰል ጥይቶቻቸው ጋር ተማርከዋል፡፡ በአጠቃላይ ምርኮው ወደ አዲስ አበባ የተጓጓዘው በአምስት መቶ አጋሰሶች ተጭኖ ነው።

ታላቁ የጥቁር ህዝቦች ድል በመላው ዓለም ፖለቲካ ላይ ከፍተኛና ዋነኛ ለውጦች አምጥቶአል። የእንግሊዝ ጋዜጦች በአድዋ ድል ማግስት “የዓለም ታሪክ ተገለበጠ፤ታላቅ የትውልድ ኃይል በአፍሪቃ ተቀሰቀሰ” ብለው ፃፉ። በኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ፡- ዘመናዊት ኢትዮጵያን የፈጠረ የተባሉት ዳግማዊ ዓፄ ምኒሊክ በሌሉበት (እርሳቸው በአካል ባልተገኙበት የነፃነት ተጋድሎ መሪዎች ጉባኤ) የአፍሪቃና የመላው ዓለም ጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተጋድሎ መሪ ተደርገው ተመረጡ። ከፈረንጅ የአውሮጳ መንግሥታት ሩሲያና ፈረንሳይ የአድዋን ድል ከልብ ደገፉ።

ጀኔራል ባራቴሪ በአገሩ በኢጣሊያ ጦር ፍርድ ቤት ቀርቦ ማዕረጉ ተገፈፈ። የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲኞር ክሪስፒ በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ለቀቁ።

የኢጣሊያዊው ንጉሥ አማኑኤል ኡምቤርቶ የልደት ቀን የሀዘን ቀን እንዲሆን ተወሰነ።ሮምን ጨምሮ ሌሎች የኢጣሊያ ትላልቅ ከተሞች "ምኒሊክ ለዘላለም ይኑር" በሚሉ የተቆጡ አውሮጳውያን ትዕይንተ ህዝብ አድራጊዎች ተጥለቀለቁ። ኢትዮጵያ በአድዋ ጦርነት ወቅት በዋናው የጦር ግንባር ገጥማ በፍልሚያ ድል ማድረግ ብቻ ሳይሆን በጦርነት እና በወታደራዊ መረጃ፣በዲፕሎማሲና በፖለቲካ ጥበብ ሰልጥናለች በምትባለው ኢጣሊያ ላይ ድል ተቀዳጅታለች።

የአድዋ ድል ለመጀመሪያ ጊዜ የተከበረው በሠባተኛ ዓመቱ በ1895 ዓ.ም አሁን ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ያለበት ሥፍራ ምኒሊክ አደባባይ ላይ ነው። በድል በዓሉ ላይ ዲፕሎማቶችና የውጪ አገር መንግሥታት ተወካዮች፣አርበኞች፣የመንግስት ባለሥልጣኖች፣ብዙ ሺህ ፈረሰኞችና ወፈሠ ማይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ከሊቅ እስከ ደቂቅ መገኘታቸውንና ከፈረሰኞቹ ብዛት የተነሳ ፀሐይ በአቧራ እስከመጋረድ መድረሷን ጳውሎስ ኞኞ የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ጦርነት በተሰኘ መጽሐፉ ላይ ጽፎአል። እንዲሁም ተክለ ፃዲቅ መኩሪያን የመሳሰሉ ኢትዮጵያውያን የታሪክ ተመራማሪዎችና የውጪ አገር ዜግነት ያላቸው ፀሐፍትና ተመራማሪዎች በተለያዩ መፃሕፎቻቸው ይሄንን አሣምረው ጽፈውታል።

እነሆ ዘንድሮም 129ኛው የአድዋ ድል በዓል "ዓድዋ የጥቁር ሕዝቦች ድል!" በሚል መሪ በተለያዩ የአደባባይና የቤት ውስጥ ዝግጅቶች በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል። በዚህ መሪ ቃል የታሰበውም አያቶቻችን ባርነትንና ቅኝ ተገዥነትን እምቢ አሻፈረኝ ብለው የቋንቋ፤ የኃይማኖት፣ የፆታና የባህል ልዩነት ሳይበግራቸው ለእናት ሀገራቸው ነፃነትና ክብር ሕይወታቸውን ያለመሳሳት የሰጡበት፣ኢትዮጵያውያን ጀግኖች በአፍሪካ ምድር በክቡር ደማቸውን ያፈሰሱበት፤አጥንታቸውን የከሰከሱበትና የዛሬ ነፃነትን ሚስጥር በአድዋ ተራሮች ላይ የጻፉበት በመሆኑ ነው። በዚህም የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በአፍሪካና በመላው ዓለም ደምቃና ከብራ ከፍ ብላ ከመታየቷ ባሻገር በልጆቿ ተጋድሎና ቆራጥነት በዓለም የነፃነት ምድር፣የጥቁር ህዝቦች የአይበገሬነት ተምሳሌት ሆና ቀጥላለች።

በመጨረሻም በአሉን ስናከብር የአድዋ ድል በዓለም አቀፍ ታሪክ ውስጥ የፈጠረውን ልዩና አዲስ ታሪካዊ ምዕራፍ በመከተል የአሁኑ ትውልድ ከአባቶቹ የወረሰውን ታላቅ የአገር ፍቅር፣ነፃነትና አንድነት በተግባር ማሳየት ሊሆን ይገባል። ይህን ለማሳየት ደግሞ አባቶቻችን

የጦር ግንባር መስዕዋት ሆነው ያስረከቡንን ነጻነት፣አገር ክብርና ዝና ለመጠበቅ፤በተሰማራንበት የስራ ዘርፍ ሁሉ ጠንክረን በመስራት ከድህነት የተላቀቀችና የበለጸገች ኢትዮጵያን መገንባት ይጠበቅብናል፡፡